የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን የካቲት 11 ቀን 2018 ዓ.ም ባካሄደው 1ኛ አስቸኳይ ስብሰባ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የአራት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አዳምጧል፡፡

እንዲሁም መጋቢት 15 እና 24 2018 ዓ.ም ባካሄዳቸው መደበኛ ሰብሰባዎች ምክር ቤቱ የተለያዩ የብድር ስምምነቶችንና ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ያጸደቀ ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርአት እና የማስረጃ ሕግ መርምሮ አጸደቋል፡፡

የየካቲት እና የመጋቢት ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎችን አበይት ምክር ቤታዊ ጉዳዮች ታስነብባለች፡፡

## ዓበይት ርዕሶች

- ህግ አወጣጥ
- ክትትል ቁጥጥር

መልካም ንባብ!
መጋቢት፣ 2018ዓ.ም

## ክትትል ቁጥጥር

6ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ የካቲት 11 ቀን 2018 ዓ.ም 1ኛ አስቸኳይ ስብሰባውን አካሂዷል፡፡ በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የአራት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አዳምጧል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ባለፉት አራት ዓመታት ኮሚሽኑ የሠራቸውን ሥራዎች ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በሀገር ውስጥና በውጭ የተካሄዱ የአጀንዳ ማሰባሰብና የተሳታፊ ልየታ ተግባራትን በዝርዝር ለምክር ቤቱ አቅርበዋል።





የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሲያቀቀርቡ

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄና አስተያየቶች ምላሽ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው በተለይም የምክክር ሂደቱ የትግራይ ክልልን ጨምሮ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ከማሳተፍ አኳያ፣ በሀገሪቱ በአንዳንድ አካባቢዎች ያለው የጸጥታ ሁኔታ በምክክር ሂደቱ ላይ እያሳደረ ያለው ተጽዕኖ እና ኮሚሽኑ ሂደቱን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ለማጠናቀቅ ስላለው ዝግጅት ጥያቄዎችና አስተያየቶች አንስተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄና አስተያየቶች ምላሽ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በምክር ቤቱ የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ እውነቱ አለነ የምክክር ኮሚሽኑ ባለፉት ዓመታት ለቀጣይ የምክክር ሂደቱ ተግባራት ወሳኝ መሠረት የሚጥሉ ሥራዎችን ማከናወን መቻሉን ገልጸው በቀጣይ ኮሚሽኑ ታላቁን ሀገራዊ የምክክር ጉባኤ እንዲጀምርና ከምክክሩ የሚገኙ ምክረ-ሐሳቦች ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ በሚያስችል መልኩ ቀሪ ሥራዎችን እንዲያጠናቅቅ ተጨማሪ የስምንት ወራት ጊዜ እንዲሰጠው ለምክር ቤቱ ያቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ በሙሉ ድምጽ ጸድቋል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ስኬት እንደሀገር ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚጠቅም መሆኑን ገልጸዋል፡፡





ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ጥንታዊ እና ረጅም ታሪክ ካላቸው ሀገሮችና ሕዝቦች ተርታ የምትመደብ ብትሆንም በሀገረ መንግሥት ግንባታ ውስጥ የሚታዩ ከትላንት የተሻገሩ እስከ ዛሬ ድረስ የዘለቁ ስብራቶች መኖራቸው የሚፈለገው ሀገራዊ ከፍታ ላይ ለመድረስ የማያስችሉ ታሪካዊ መሰናክሎች መኖራቸውን በተለያዩ ዜጎች ጭምር የሚነሳ ሐሳብ ነው ብለዋል፡፡
ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር ዋና ዋና በሆኑ መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት አለመፍጠራቸው ትልቅ ስብራት ሆኖ መቆየቱን አንስተው በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት የታዩ ስብራቶችን ለመጠገን እንዲቻልና የጋራ መግባባት ለመፍጠር ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ መቋቋሙ ወቅታዊ እና አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡ የምክክር ኮሚሽኑ ባለፉት አራት ዓመታት ሊሂቃንን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጋ ባሳተፈና ሁሉም ሀሳቡን በሚያዋጣበት መልኩ ምክክር በማድረግ ግቡን በሚያሳካ ሁኔታ በርካታ ሥራዎች መሥራቱን እና በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በሒደቱ መሳተፋቸውን አክለው ገልፀዋል።

በመጨረሻም የተከበሩ አፈ ጉባኤ  አቶ ታገሰ ጫፎ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ ስራዎችን ያከናወነ መሆኑን አንስተው ሀገራዊ ምክክሩ በቀጣይ ጊዜያት በሁሉም ክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉ ዜጎች በሀገራዊ ጉባኤ የሚሳተፉበት ሁኔታ ተለይቶ የሚሰራ ሲሆን የትግራይ ክልልን የምክክሩ ሂደት ተሳታፊ ለማድረግ የተጀመረውን ተሳታፊዎችን የመለየትና አጀንዳ የማሰባሰብ ሥራ ዳር ማድረስ ሀገር የማፅናት ጉዳይ በመሆኑ የምክር ቤት አባላት እንዲሁም መላው ኢትዮጵያውያን የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡

በመጨረሻ ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን የሥራ ዘመን ለ8 ወራት ተጨማሪ ጊዜ እንዲራዘም የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ የውሳኔ ቁጥር 8/2018 በማድረግ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

## ሕግ አወጣጥ

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አምስተኛ ዓመት የስራ ዘመን መጋቢት 15፣ 2018 ዓ.ም በአካሄደው አስራ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባውን አካሂዷል፡፡

በዕለቱም የተለያዩ የብድር ስምምነቶችን አጽድቋል።



ምክር ቤቱ በውሎው በኢትትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኮሪያ ኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወዳጄ ለምክር ቤቱ በንባብ አቅርበዋል፡፡

የተከበሩ አቶ ደሳለኝ የብድሩን አስፈላጊነት ሲያብራሩ የህክምና ተቋማትን በተሟላ ግብዓቶች በማደራጀትና የህክምና መሳሪያዎች ችግር ለመፍታት፣ የጤና አገልግሎቱን ለማሻሻል እንዲሁም የአቅርቦቱን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት መንግሥት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በተለይም ከለጋሽ ሀገራትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና ከሌሎች የጤና ድጋፍ ሰጪ አጋሮች ጋር በትብብር በመስራት የተቀናጀ የጤና ስርዓት በመዘርጋት ለህብረተሰቡ የተሻለ የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

በብድር በስምምነት የተገኘው ገንዘብ 0.05 በመቶ ወለድ የሚከፈልበት እና አስራ አምስት ዓመት የችሮታ ጊዜ ያለው ሆኖ በረጅም ጊዜ (በአርባ ዓመታት) ውስጥ የሚከፈል እንደሆነና ከሀገራችን የብድር ስልት ጋር የሚጣጣም መሆኑን አንስተዋል፡፡



ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ ጥልቅ ውይይት በማድረግ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1406/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።

በተያያዘም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኮርያ ኤክስፖርት -ኢምፖርት ባንክ መካከል ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ተጨማሪ የብድር ስምምነትን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) የብድር ስምምነቱን አስፈላጊነት ለምክር ቤቱ ገልጸዋል፡፡





የተጨማሪ ብድር ስምምነቱ 60,223,000.00 (ስልሳ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር ሲሆን የብድር ስምምነቱ በዓመት 0.01 በመቶ ወለድ የሚከፈልበት መሆኑ ተብራርቷል፡፡ ሆኖም ግን ከኮርያ አቅራቢዎች የሚገዛ ከሆነ ከወለድ ነፃ እንደሆነና የአገልግሎት ክፍያ 0.1 በመቶ ለባንኩ የሚከፈል ሲሆን የአስራ አምስት ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ40 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ እንደሚጠናቀቅ ገልጸው የብድር ስምምነቱ ከሀገራችን የብድር ስትራቴጂ ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ቀላል ብድር መሆኑንም ጠቁመዋል።

የቀረበው ሞሽን ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግሮ ምክር ቤቱ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1407/2018 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።

ሌላው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ለታዳሽ፣ የተቀናጀ፣ ዘላቂ ኃይል እና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበ ረቂቅ አዋጅ በማስመልከት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) ለምክር ቤቱ ገለፃ አድርገዋል።

የብድሩ መጠን 80,000,000.00 (ሰማኒያ ሚሊየን) ዩሮ መሆኑን የገለጹት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የብድር ስምምነቱ በየዓመቱ 1.2 በመቶ ወለድ የሚከፈል ሲሆን 0.5 የአገልግሎት ክፍያን የሚያካትት፣ ሰባት ዓመት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ20 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚያልቅ መሆኑን አብራርተዋል።

የቀረበው ሞሽን ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግሮ ከምክር ቤቱ አባላት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ቀርው ጥልቅ ውይይት ተደርጎበታል፡፡

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ለታዳሽ፣ የተቀናጀ፣ ዘላቂ ኃይል እና ዲጂታላይዜሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የቀረበው ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1408/2018 ሆኖ በሙሉ ድምጽ በምክር ቤቱ ጸድቋል።

በተመሳሳይ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔትና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ሶስተኛ ተጨማሪ የብድር ስምምነት ምክር ቤቱ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል። በምክር ቤቱ የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትሩ የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔትና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ሶስተኛ ተጨማሪ የብድር ስምምነት የ184,000,000.00 (አንድ መቶ ሰማኒያ አራት ሚሊየን) የአሜሪካን ዶላር ከወለድ ነጻ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የተገኘው ብድር የስድስት ዓመታት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ30 ዓመታት ውስጥ የሚከፈል መሆኑንም ለምክር ቤቱ አብራርተዋል። የምክር ቤት አባላት በበኩላቸው የብድር ስምምነቶች ለታለመላቸው ዓላማ ውለው የዜጎችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ እና ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ የእድገት ደረጃ ለማሸጋገር የሚያግዙ እንዲሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግባቸው እንደሚገባ አሳስበዋል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE





በኢፌዲሪ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ድኤታ ክብርት ወ/ሮ ሠመሪታ ሰዋሰው በበኩላቸው የብድር ስምምነቶች በየዘርፉ ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ እንዲውሉና ግባቸውን እንዲመቱ ክትትሎች የሚደረጉ መሆኑን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል።

ሞሽኑ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግሮ ምክር ቤቱ በስፋት ከተወያየበት በኋላ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ለከተማ ልማታዊ ሴፍትኔትና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተደረገውን ሶስተኛ ተጨማሪ የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አዋጅ ቁጥር 1409/2018 ሆኖ በሙሉ ድምጽ ጽድቋል።
ምክር ቤቱ በዕለቱ ከያዛቸው አጀንዳዎች መካከል የጉምሩክ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የቀረበውን ረቂቅ አዋጅ ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መምራት ሲሆን የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ ተስፋዬ በልጅጌ (ዶ.ር) ስለ ረቂቅ አዋጁ መሻሻል አስፈላጊነት ገለፃና ማብራሪያ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው በመወያየት ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 9/2018 ዓ.ም ሆኖ ለዝርዝር እይታ ለፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሙሉ ድምፅ መርቶታል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

## 6ኛው የኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 24 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 13ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢ.ትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርአት እና የማስረጃ ሕግ መርምሮ አጸደቀ፡፡





የረቂቅ ሕጉን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ የህግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት መንግሥቱ አቅርበዋል፡፡

የኢ.ፌዲሪ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርአት እና የማስረጃ ረቂቅ ሕግ የሕገ መንገሥቱ ግቦች የሆኑት የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ ሠላምና ልማትን ማምጣት ሊሳኩ የሚችሉት የሃገር፣ የሕዝብና የግለሰቦች ሠላምና ደህንነት ሲጠበቅ በመሆኑ መንግሥት በዚህ መልኩ የሚገለፁትንና መሠረታዊ የሆኑትን የግለሰብና የቡድን መብት እና ጥቅም የማሟላት፣ የማክበርና የማስከበር ግንባር ቀደም ኃላፊነት ተጥሎበታል ሲሉ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ ባቀረቡበት ወቅት ገልጸዋል፡፡

ረቂቅ ሕጉ የኢ.ፌዲሪ ሕገ መንግሥትን እና ኢ.ትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ መርሆዎችን እና እሴቶችን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ለሀገሪቱ የዲሞክራሲ ሥርአት ግንባታ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችልና የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርአትን ለማዘመን የሚደረገውን ጥረት ያግዛል ሲሉ የተከበሩ ወ/ሮ እጸገነት አስገንዝበዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

አክለውም በወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርአቱ በተጠርጣሪ፣ በተከሳሽና በተጐጂዎች ላይ የሚደርሰውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በማስቀረት እና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን በማድረግ አዎንታዊ ሚና የሚጫወት፤ ሁሉንም ዜጐች በእኩልነት የሚዳኝ ሲሆን አገሪቱን የጠንካራ ፍትህ ተቋም ባለቤት በማድረግ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አበርክቶት አለው ብለዋል፡፡

አሁን ሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ስርአት ላይ የሚታዩ በርካታ ጉድለቶችን የሚቀርፍ፤ በዘመኑ ከሚፈጸሙት ውስብስብና የረቀቁ ወንጀሎች አንጻር እንዲሁም ዘመኑ ከደረሰበት የወንጀል ሳይንስ ጋር የተጣጣሙ በርካታ ድንጋጌዎች የተካተቱበት እና የአገራችንን የፍትህ ሥርአት በማዘመን ሂደት ጉልህ አስተዋጽኦ ያለው የሕግ ማእቀፍ ነው ሲሉ ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡





ምክር ቤቱም በረቂቅ ህጉ ላይ ጥልቅ ውይይት ካደረገ በኋላ የኢ.ፌዲሪ የወንጀል ሕግ ሥነ-ስርአት እና የማስረጃ ረቂቅ ሕግን በአዋጅ ቁጥር 1410/2018አድርጎ በሁለት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል፡፡





የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

## ለበለጠ መረጃና አስተያየት


አድራሻ (Address)

ስልክ Tel:- 011-154-52-33
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ.ሜይል E-mail info@hopr.gov.et


በኢ.ፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፤ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፤

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE